- የእግዚአብሔር መንገድ

- የእግዚአብሔርን መንገድ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት።



## ትምህርት 35

1. እግዚአብሔር ለሙሴ አሥርቱን ትእዛዛት በሰጠበት ጊዜ ሙሴ አንድ ነገር እንዲሠራለት አዝዞት ነበር። ሙሴ እንዲሠራለት እግዚአብሔር ያዘዘው ነገር ምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ሙሴን የመገናኛ ድንኳን እንዲሠራለት አዘዘው።

2. እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት ያስፈልገዋል?

ሀ- አያስፈልገውም።

3. እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ነው።

ለ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ ስለሚገኝ ነው።

4. እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

ሀ- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ የሚጠብቁ ከሆነ እንደሚባርካቸው ትእዛዛቱን ሁሉ የማይጠብቁ ከሆነ እንደሚቀጣቸው።

5. እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ ችለዋል?

ሀ- አልቻሉም።

6. እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

ሀ- አዎን።

7. ከትእዛዛቱ አንዷን እንኳን ለሚጥሱ የእግዚአብሔር ቅጣት ምንድን ነው?

ሀ- ሞት በዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

8. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያዘጋጀላቸው የማምለጫ መንገድ ምን ነበር?

ሀ- እስራኤላውያን ኃጢአት በመስራት ከእግዚአብሔር ሕግጋት አንዱን በሚጥሱበት ጊዜ ሁሉ ወደ መገናኛው ድንኳን ሄደው የእንስሳት ደም ያቀርባሉ።

9. እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ምን ያደርጋል?

ሀ- እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ለኃጢአት የተሻለ ዋጋ እስኪከፈል ድረስ እስራኤላውያንን ከመቅጣት ይታቀባል።

10. እግዚአብሔር ሙሴና እስራኤላውያን ድንኳን እንዲሠሩለት የፈለገው እንዴት ነበር?

ሀ- ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት።

11. እግዚአብሔር ሙሴ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዲሠራ ያዘዛቸው ሁለት ክፍሎች ምንና ምን ይባሉ ነበር?

ሀ- ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ይባሉ ነበር።

12. እግዚአብሔር ሙሴ ሠርቶ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ እንዲያስቀምጥለት ያዘዘው ልዩ ሳጥን ምን ነበር?

ሀ- የቃል ኪዳኑ ታቦት።

13. ቅድስትንና ቅድስተ ቅዱሳኑን የሚለየው መጋረጃ ምንን የሚያመለክት ነበር?

ሀ- መጋረጃው እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር መለያታቸውን ያስተምር ነበር።



43- ሙሴ ሥራውን አየ፤ ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው መሥራታቸውንም ተመለከተ፤ ስለዚህ ባረካቸው።

17- እንዲሁም በሁለተኛው ዓመት፣ የመጀመሪያው ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን የማደሪያው ድንኳን ተተከለ።

- እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት የማደሪያውን ድንኳን ስለ ሠሩ የእግዚአብሔር ክብር ወደ ድንኳኑ ገባ።

ዘጸአት 40፡34-35

34- ከዚያም ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ሸፈነ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ።

35- ደመናው በላዩ ላይ ስለ ነበረና የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ስለሞላው፣ ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን መግባት አልቻለም።

- እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት የማደሪያውን ድንኳን ባይሠሩ ኖሮ የእግዚአብሔር ክብር በድንኳኑ ውስጥ ይገባ ነበር?

- አይገባም።

- እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት የማደሪያውን ድንኳን ስለ ሠሩት የእግዚአብሔር ክብር ድንኳኑን ሞላው።

- እስራኤላውያን በራሳቸው መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ችለዋል?

- አልቻሉም።

- እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ ምን ነበር?

ላይ በተነውና እስራኤላውያን እንዲጠጡት አስገደዳቸው።

- ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ሁለት የምስክር ጽላቶች ስለ ሰባበራቸው እግዚአብሔር ሙሴን ምን አድርግ አለው?

ዘጸአት 34፡1-2

1- እግዚአብሔር ሙሴን አለው፤ «እንደ መጀመሪያዎቹ ያሉ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጥረብ፤ እኔም አንተ በሰበርካቸው በመጀመሪያዎቹ ጽላቶች ላይ የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ።

2- በማለዳ ተዘጋጅተህ ወደ ሲና ተራራ ውጣ፤ በዚያ በተራራው ጫፍ ላይ በፊቴ ቁም።»

- እግዚአብሔር ሙሴ ሌሎች ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠርቦ በድጋሚ ዐሥርቱን ትእዛዛት እዲጽፍባቸው ወደ ተራራው እንዲያመጣቸው ነገረው።

- በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር በድጋሚ ዐሥርቱን ትእዛዛት በአዲሶቹ ጽላቶች ላይ ጻፈ።

- እግዚአብሔር ሙሴን «እስራኤላውያን የመገናኛ ድንኳን ይሥሩልኝ» ብሎ የነገረውን ታስታውሳላችሁ?

- ከጥቂት ጊዜ በኋላ እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ድንኳን ሠሩ።

ዘጸአት 39፡42-43 & 40፡17

42- እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ሥራውን ሁሉ አከናወኑ።



14. እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለመሥዋዕት በሚያቀርቡት እንስሳ ራስ ላይ እጃቸውን እንዲጭኑ ያዘዘው ለምን ነበር?

ሀ- እስራኤላዊው ለመሥዋዕት በሚያቀረበው እንስሳ ራስ ላይ እጁን የሚጭነው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱንና ሞት የሚገባው መሆኑን ለመግለጽ፥ እግዚአብሔር ግን የሰውየውን ሞት ሳይሆን የእንስሳውን ሞት እንዲቀበል ነበር።

15. የእንስሳት ደም የእስራኤላውያንን የኃጢአት ዋጋ መክፈል ይችላል?

ሀ- አይችልም።

16. ካልቻለ እግዚአብሔር ለምን ነበር እስራኤላውያን ስለ ኃጢአታቸው እንስሳትን እንዲሠዉ የጠየቃቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነበር።

17. እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ምን ያደርግ ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ፍጹም የሆነ የደም መሥዋዕት እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ እስራኤላውያንን ከመቅጣት ይታቀብ ነበር።

18. አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንዲገባ እግዚአብሔር የመረጠበት ቀን ሲደርስ ምን ይዞ እንዲገባ አዘዘው?

ሀ- እግዚአብሔር አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚገባበት ጊዜ የእንስሳ ደም ይዞ እንዲገባ አዘዘው።

19. እግዚአብሔር ያዘዘውን አሮን ካደረገና በኪዳን ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ ደም ከረጨ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

ሀ- እግዚአብሔር የተሻለ የኃጢአት መሥዋዕት እስኪቀርብ ድረስ ለተጨማር አንድ አመት እስራኤላውያንን ከመቅጣት ይታቀባል።

- ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ላይ ሳለ እስራኤላውያን በተራራው ግርጌ ምን ያደርጉ ነበር?

ዘጸአት 32፥1-6

1- ሕዝቡ ሙሴ ከተራራው ላይ ሳይወርድ ብዙ እንደ ቆየ ባዩ ጊዜ፣ ወደ አሮን ተሰብስበው፣ «ናና በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን፤ ያ ከግብፅ ያወጣን ሙሴ ምን እንዳገኘው አናውቅም» አሉት።

2- አሮንም፣ «የሚስቶቻችሁን፣ የወንድና የሴት ልጆቻችሁን የጆሮ ወርቅ አውልቃችሁ ወደ እኔ አምጡ» ብሎ መለሰላቸው።

3- ሕዝቡም ሁሉ የጆሮ ወርቃቸውን አውልቀው ወደ አሮን አመጡ።

4- እርሱም የሰጡትን ወስዶ በመሣሪያ በመቅረጽ በጥጃ ምስል ጣዖት አድርጎ ሠራው፤ ከዚያም እነርሱ፣ «እስራኤል ሆይ፤ ከግብፅ ያወጡህ አማልክት እነዚህ ናቸው» አሉ።

5- አሮን ይህን ባየ ጊዜ በወርቅ ጥጃው ፊት ለፊት መሠዊያ ሠርቶ፣ «ነገ ለእግዚአብሔር በዓል ይሆናል» ብሎ ዐወጀ።

6- በማግሥቱ ሕዝቡ በማለዳ ተነሥተው የሚቃጠል መሥዋዕት ሠው፤ የኅብረት መሥዋዕት አቀረቡ፤ ከዚህም በኋላ፣ ይበሉና ይጠጡ ዘንድ ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ።

- እስራኤላውያን በተራራው ግርጌ ምን ያደርጉ ነበር?

- እስራኤላውያን ከወርቅ ጥጃ ሠርተው ያመለኩ ነበር።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ምን ነበር?



- ሙሴ ከሲና ተራራ ግርጌ እንደ ደረሰ ምን አደረገ?

ዘጸአት 32፥15-19

15- ሙሴም ሁለቱን የምስክር ጽላቶች በእጆቹ ይዞ ከተራራው ወረደ፤ ጽላቶቹም ከፊትና ከኋላ በሁለት ወገን ተጽፎባቸው ነበር።

16- ጽላቶቹ የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፤ በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸው ጽሕፈትም የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር።

17- ኢያሱ የሕዝቡን የጩኸት ድምፅ በሰማ ጊዜ ሙሴን፣ በሰፈሩ ውስጥ የጦርነት ድምፅ አለ» አለው።

18- ሙሴም «የድል ድምፅ አይደለም፤ የሽንፈትም ድምፅ አይደለም፤ የምሰማው የዘፈን ድምፅ ነው» ብሎ መለሰለት።

19- ሙሴ ወደ ሰፈሩ ደርሶ ጥጃውንና ጭፈራውን ባየ ጊዜ ቁጣው ነደደ፤ ጽላቶቹን ከእጁ በመወርወር ከተራራው ግርጌ ሰባበራቸው።

- ሙሴ በእስራኤላውያን ላይ በጣም ስለ ተናደደ የእግዚአብሔር ትእዛዛት የተጻፈባቸውን ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ወርውሮ ሰባበራቸው።

- ቀጥሎስ ሙሴ ምን አደረገ?

ዘጸአት 32፥20

20- የሠሩትን ጥጃ ወስዶ በእሳት አቃጠለው፤ ከዚያም ዱቄት እስኪሆን ፈጨው፤ በውሃ ላይ በተነው፤ እስራኤላውያንም እንዲጠጡት አደረገ።

- ሙሴ የወርቁን ጥጃ ሰባበረው ወርቁን ወደ ዱቄትነት ለወጠው በውኃውም

12- ግብፃውያን 'በተራራዎቹ ላይ ሊገድላቸው ከገጸ ምድርም ሊያጠፋቸው ስለ ፈለገ ነው ያወጣቸው' ለምን ይበሉ? ከክፉ ቁጣህ ተመለስ፤ ታገሥ በሕዝብህም ላይ ጥፋት አታምጣ።

13- ለባሪያዎችህ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለእስራኤል፣ 'ዘርህን እንደ ሰማይ ክዋክብት አበዛዋለሁ፤ ለዘርህም ተስፋ አድርጌ የሰጠኋቸውን ይህችን ምድር ሁሉ እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም ርስታቸው ትሆናለች' በማለት በራስህ የማልኸውን አስታውስ። »

14- ከዚያም እግዚአብሔር ታገሠ፤ በሕዝቡም ላይ አመጣባቸዋለሁ ያለውን ጥፋት አላመጣባቸውም። »

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ ያላጠፋቸው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያን እንዳያጠፋቸው ስለ ጸለየ ነው።

- ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው ለማድረግ ምን አለ?

- ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ካጠፋ «ግብፃውያን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ያወጣቸው ሊገድላቸው ነው» ይላሉ አለ።

- ሙሴ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ «ዘራችሁን አበዛለሁ ታላቅ ሕዝብም አደርጋችኋለሁ። » ብሎ የገባውን ቃል እንዲጠብቅ ለመነ።

- ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ስለ ጸለየ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አላጠፋቸውም።

- ከዚያም ሙሴ ከተራራው ጫፍ ወደ ታች ወረደ።



- የሰው ሁሉ አምላክ መሆን ያለበት እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚል ነበር።

- እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ያስቀደሙት ነገር ነበራቸው?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ሁለተኛው ትእዛዝ ምን ነበር?

- ማንም ሰው ማንኛውንም ምስል መሥራትም ሆነ ማምለክ የለበትም የሚል ነበር።

- እስራኤላውያን ምስል ሠርተው አመልከዋል?

- አዎን።

- ከጥቂት ቀናት በፊት እስራኤላውያን «እግዚአብሔር ያዘዘንን ትእዛዛት ሁሉ እንጠብቃለን» ብለው ነበር።

- አሁን ግን እስራኤላውያን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሁለቱን ትእዛዛት እየተላለፉ ነው።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ያመጣቸውን አሥር መቅሰፍቶች አይተው ነበር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ቀይ ባህርን ከፍሎ በባህሩ መካከል እንዳሻገራቸው አይተው ነበር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ፈርዖንንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ እንዳሰመጣቸው አይተው ነበር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ድርጭትና መና ከሰማይ እንደ ላከላቸው አይተው ነበር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከዐለት ውስጥ ውኃ እንደ ሰጣቸው አይተው ነበር።

- አሁን አስራኤላውያን «ከግብፅ ያወጣን ይህ የወርቅ ጥጃ ምስል ነው» በማለት የወርቁን ጥጃ ምስል ያመልኩ ነበር።

- እስራኤላውያን የወርቁን ጥጃ ምስል እያመለኩ እንደ ነበር እግዚአብሔር አውቋል?

ዘጸአት 32፡7-8

7- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «ከግብፅ ያወጣኻቸው ሕዝብህ ስተዋልና ውረድ አለው፤ ካዘዝኳቸው ፈቀቅ ለማለት ፈጣኖች ሆኑ፤ ለራሳቸውም በጥጃ ምስል የተቀረጸ ጣዖትን ሠሩ፤

8- ለእርሱም ሰገዱለት፤ ሠዉለትም፤ እንዲሁም፣ 'እስራኤል ሆይ፤ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ እነዚህ ናቸው' አሉ።»

- እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ እያመለኩ እንደ ነበር እግዚአብሔር አውቋል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ ሲያመልኩ ተመለከቷል።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያያል።

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እንዳይበሉ ካዘዛቸው ፍሬ ሲበሉ ተመለከቷል።

- እግዚአብሔር ቃየንን አቤል ሲገድለው ተመለከቷል።



- እግዚአብሔር የሰዶምና የገሞራን ሰዎች ኃጢአት ተመለከቷል።

- እግዚአብሔር የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ለባርነት ወደ ግብፅ ሲሸጡት ተመለከቷል።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ያያል ኃጢአትን ሁሉ ይጠላል።

- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ተቆጥቶ ነበር?

ዘጸአት 32፡9-10

9- እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ «እነዚህን ሕዝብ አይቻቸዋለሁ፤አንገተ ደንዳናዎችም ናቸው፤

10- አሁንም በእነርሱ ላይ፣ ቁጣዬ እንዲነድና እንዳጠፋቸው ተወኝ፤ ከዚያም አንተን ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ።»

- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ በጣም ተቆጣ።

- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ እጅግ ስለ ተቆጣ ሊያጠፋቸው ፈለገ።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ምን አለው?

ዘጸአት 32፡11-14

11- ነገር ግን ሙሴ የአምላኩን የእግዚአብሔርን ቸርነት ፈለገ፤ እንዲህም አለ፤ «እግዚአብሔር ሆይ፣ በታላቅ ሥልጣንህና በኃያል ክንድህ ከግብፅ ባወጣኸው ሕዝብህ ላይ ቁጣህ ለምን ይነዳል?